

የኔ እናት ልዩ ናት

እምዬ የኔ እናት የመኖሬ ምስጢር

ምል በል ስላንቺ ከየቱስ ልጀምር ።

ከ ሀ እስከ ፐ ባሉት ፊደሎች በሙሉ

ሺህ ቃል ቢመሰረት ጠቢባን በተባሉ

አንቺን አይገልፅሽም ለፍቅርሽ ያንሳሉ።

በልዩ ሀብረት ቃል ስላንቺ ቢያወሩ

የማያልቅ ሆኖ ነገር ..... ጀምረውት ቀሩ ።

የእናትነት ፍቅርሽ እጹብ ድንቅ እኮ ነው

ህይወቴን በሙሉ ላንቺ ብሰራ ሸ

ነብሴን ሳልሳሳ ሳልሰስት ብሰዋ ሽ

ካረግሽልኝ ነገር ከዛ ሁሉ

አንዱንም አይተካም

ስለዚህ የኔ እናት ልዩ ና

ውለታሽ በዝቶብኝ ሆኖብኝ ተራራ

እናቴ ምን ልበልሽ ስላንቺስ ምን ላ

እናቴ ምነው ዘንደሮስ ጨከነሽብኝ

ምነው እናቴ ይሄ ዓመት ጨከነሽ

ድምጽሽን ለመስማ ናፍቆኛ

አናግሪኝ እናቴ ደስ በሚለው ቁጣ

ዛሬ ሳትደውይልኝ ቀድሜሽ ብመጣ

በዛውም ያልሸኘን ገዝቼ ብመጣ።

ዝም አልሽ እኮ እማ .....

ያ ምርቃትሽ ያ ማሞካሻ ቃላቶችሽ

እማዬ እናቴ የት ጥለውሽ ሄዱብሽ ።



የዛለት ቀን ነበር ህመምሽ ያየውት ቀን

ሰማይ ምድሩ ነበር የዞረብኝ በዛን ቀን ።

እናቴን አደራ ብዬ ነግሬው ለአምላኬ

እሱም ሰምቶኝ ነበር በመጀመሪያዉ ቀን

ከአሁን አሁን እማ ትድኛለሽ ብዬ እየጠበኩኝ

የህኪሞች ምላሽ ተስፋ አስቆረጠኝ ።

ሁሌም የምሳሳሽ ነበርሽ አንድ እናቴ

መኖርሽ ያኖረሽ ባንቺ ሰው የሆንኩት

በፍቅርሽ በሳቅሽ ነበር የተዋብኩት

በስምሽ ያጌጥኩ ባንቺ የደመቅኩት ።

እንደት ነው የምኖረው ካንቺ ዓይቼ

መች ሰው እሆናለው አንቺ ሳይቼ ።

ሳቅና ደስታዬ ባንቺ ላ

ጥለሽኝ ስትሄጂ አብረ

እኔም ለልደትዬ ነግሬ ነበረ

ሁሉም ሳይሳካ በመቃብር ቀረ ።

አሁን ብትሄጂ ርቀሻል ከኔ

ሁሉም ጨለመብኝ ጠፋ ብ

እኔም ያቅሜን ነበ

ግን ማዳን አልቻልኩም ቀረውኝ ዋትቼ ።

ምነው ፈጣሪዬ ጸሎቴን ብትሰማ

ማርልኝ ብዬ ነው የደከምኩት እማ ።

ነገር ግን አልሆነው የኔ ከንቱ ልፋት

ሞት የሚባለው ጨካኝ እናቴን ወሰዳት ።

ነገር ግን እናቴን አምላኬ ቢወስዳት

ዛሬም ነገም ለዘለዓለም

በልቤ ውስጥ ትኖሪያለሽ ።

😭😭😭😭😭😭😭

ቸሩ ፈጣሪዬ በገነት ያኑራት ።።

